# የጥንቷ የካቶሊክ ንጉሠ ነገሥታዊ ቤተ ክርስቲያን የበላይነት 313-590 ዓ.ም.

## ምዕራፍ II

## የቤተ ክርስቲያን ከመንግሥትና ከባርቢሪያንስ ጋር መቋቋም

1101. የጭለማው ዘመን በሚባል የሚታወቀው ከ375-1066 ዓ.ም. የነበረው ጊዜ የባርቤሪያን ቲዩቶኒክ ነገዶች (የጀርመንና የእንግሎ ሳክሰን ዝርያዎች) እንቅስቃሴ በምዕራብ አውሮፓ የተስፋፋበት ዘመን ሲሆን፥ በዚህ የታሪክ ወቅት ቤተ ክርስቲያን ሁለት ይዘት ያለው ችግር ገጥሟት ነበር። በትድሚያ የሮም መንግሥት ለመውደቅ በተቃረበበት በዚያ ዘመን ቤተ ክርስቲያንም በበኩሏ በመበስበስ ብሉም በመፈራረስ ላይ የሚገኘውን የግሪክ-ዕብራውያን ባህል እንደ 'ጨው' ሆና የማቆየቱ ኃላፊነት ከፊቷ ተደቅኖ ነበረ። ይህንንም ከባድ ኃላፊነት በመወጣት ረገድ፥ ቅዱሳት መጻሕፍት በከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠበቁባቸውና የመጻሕፍቶቹም የእጅ ቅጂዎች የሚረቡባቸው ገዳማት የላቀ የሥራ ድርሻ አበርክተዋል። ቤተ ክርስቲያንን ያሳሰባት ሌላው ኃላፊነት ደግሞ በብዛት በመንከራተት ላይ ለሚገኙት ዘላኖች፥ እራሷን 'ብርሃን' በማድረግ ወንጌልን እንዴት ለመስበክ እንደምትችል ነበር። ቤተ ክርስቲያን ይህንን ኃላፊነቷን የተወጣችው ሚሲዮናዊ በሆኑ መነኩሳት በኩል ሲሆን ሁሉንም ነገዶች ለክርስትና እምነት በማሸነፍ አጅግ ተሳክቶላት ነበር። ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያን ባህሏን ለመጠበቅና የተለያዩ ነገዶችን ወደ ክርስትና እምነት ለመለወጥ ላገኘችው የተሳካ ውጤት መሥዋዕትነት መክፈል ነበረባት። ከእነዚህም ዋነኞቹ የመንግሥትን በውስጥ ጉዳይዋ ጣልቃ ገብነት አሜን ብላ መቀበልና ዓለማዊ የአስተዳደር ፈለጎችን ለመከተል መገደድዋን ሲሆን፥ በዚህ ሳቢያ የድርጅታዊ አወቃቀር እድገቷና የትምህርት አሰጣጧ ጥራት በእያሌው ሊጎዱ በቅተዋል።

### 1. ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት

ቆስጠንጢኖስ የሃይማኖት ነጻነትን ካወጀ በኋላ በመንግሥትና በቤተ ክርስቲያን መካከል ስለነበረው ግንኙነት ለመረዳት፤ በዚያን ወቅት ንጉሠ ነገሥቱን ገጥመውት ስለነበሩት ፖለቲካዊ ችግሮች በመጠኑም ቢሆን ማወቅ ያስፈልጋል። በሮም ግዛት ውስጥ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ133-31 በነበረው ክፍለ ዘመን የተነሣው ፖለቲካዊ አለመፅ የሮምን ሪፐብሊክ ደብዛ ከማጥፋቱም፥ አውግስጦስ ባላንጣውን አንቶኒን አሸንፎ መንግሥቱን እስካዳበለበት ጊዜ ድረስ ሥርዓተ አልበኝነት መንሥኤ ሆኖ ቆይቶ ነበር። ምንም እንኳን አውግስጦስ ከምክር ቤቱ ጋር ሥልጣን በመጋራት፥ ለጊዜው ለሮም መንግሥት ከፍተኛ ብልፅግናና ሰላም ቢያስገኝም፤ ከእርሱ በኋላ ግን ሁኔታዎች እየተለዋወጡና እንደገና እየተባባሱ በመሄዳቸው ከ192-284 ዓ.ም. ያለው ሌላው ምዕተ ዓመት ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ውንብድና የተስፋፋበትና የሮም የጠረፍ ግዛቶች በወራሪ የባርቤሪያን ነገዶች የተጠቁበት ነበር። በ285 ዓ.ም. ነግሦ የነበረው ዲዮቅልጥያኖስ ግን እንደ ምሥራቃዊ ነገሥታት እራሱን ፈላጭ ቆራጭ ገዢ በማድረግ ለግሪክና ለሮም ጥምር ባህል ማንሰራራት ዋስትና ለመስጠት ሞክሮ ነበር። ሆኖም ክርስትናም ጭምር ይህንን ባህል የመፈታተን ባሕርይ እንዳለው ስላመነበት በጋሌሪዩስ አነሣሽነት ከ303-305 ዓ.ም. ባሉት ዓመታት ውስጥ ክርስትናን ለማጥፋት ከፍተኛ ጥረት አድርጎ ነበር። ከእርሱ ይልቅ ብልህ የነበረውና ቀጥሎ የነገሠው መሪ ቆስጠንጢኖስ ክርስትናን በኃይል ማጥፋት አለመቻሉን ከመረዳቱም፥ የቀድሞውን ባህል በቤተ ክርስቲያን ተባባሪነት በቀላሉ ለማዳን እንደሚቻል አመነበት። ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት መስማማት የጀመሩት ቆስጠንጢኖስ መንግሥቱን ሙሉ በሙሉ ከተቆጣጠረ በኋላ ነበር። ከ311-324 ድረስ ከሊሲኒዩስ ጋር ሥልጣን የተጋራ ቢሆንም በመንግሥት ጉዳይ ላይ ግን ተፈጻሚነት የሚያገኘውን ውሳኔ የሚያሳልፈው ቆስጠንጢኖስ ነበር።

ዘ02. (ከ274-337) የኖረው ቆስጠንጢኖስ፣ ኮንስታንቲዩስ የሚባል የአንድ የሮማ ወታደራዊ መሪ፥ ኤሌኒ ከምትባል ከምሥራቃዊው ዓለም ከመጣች ነጻና ክርስቲያን ሴት የተወለደለት ዲቃላ ልጅ ነበረ። ቆስጠንጢኖስ በ312 ዓ.ም. ላይ ጠላቶቹ ሊያሸንፉት ቀርበው ሳሉ በሰማይ ላይ የመስቀል ቅርፅ ያለው ራእይና 'በዚህ ምልክት ታሸንፋለህ' የሚል በላቲን ቋንቋ የተጻፈ ጽሑፍ ያያል። ይህም ስለወደፊቱ ሁኔታ የመልካም ዕድል አመልካች እንደሆነ በማመን በቲበር ወንዝ የሚልቪያን ድልድይ ላይ ጠላቶቹን ገጥሞ ድል ያደርጋቸዋል። ቆስጠንጢኖስ ለቤተ ክርስቲያን የነበረው በጎ አመለካከት ከዚህ ካየው ራእይ ጋር ግንኙነት ያለው ቢመስልም ለራሱ ጥቅምና ዓላማም ሲል ነው የሚል ጥርጣሬ አለ። ምናልባትም ቤተ ክርስቲያን የአንድነት አዲስ ማዕከል በመሆን ልታገለግለውና የጥንቱንም ባህል በመጠበቅ ልትረዳው እንደምትችል በማመኑም ሊሆን ይችላል። በተለይም ክርስትናን በይፋ ተቀብሎ ሳይጠመቅ ለመሞት ጥቂት እስኪቀረው ድረስ መዘግየቱና የመንግሥቱም አረማዊ ሃይማኖት የበላይ ጠባቂ የሚጠራበትን 'ፓንቲፌክስ ማክሲሙስን' ስያሜ እንደያዘ መቆየቱ ጥርጣሬውን ያጎላዋል። ከዚህም በተጨማሪ ሥልጣኑን ተቀናቅነውት የነበሩትን ወጣት ወንዶች ሁሉ መግደሉ የእውነተኛ ክርስቲያን ባሕርይ እንዳልነበረው የሚያሳይ ነው። ምናልባትም አጉል እምነትና ለራሱ ምቹ የሆነ አመራር ይከተል ነበር።

ይህ ከላይ የተሰነዘረው አስተያየት ትክክል ሆነም አልሆነም ቆስጠንጢኖስ ቤተ ክርስቲያንን የሚደግፍ ፖሊሲ (መመሪያ) አራምዷል። በ313 ዓ.ም. እርሱና የሥልጣን ታጋሪው ሊሲኒዩስ በሚላን ከተማ ባወጡት አዋጅ አማካይነት ለክርስቲያኖች ሙሉ የአምልኮ ነጻነት ተሰጧቸዋል። በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ደግሞ ቆስጠንጢኖስ ያወጣቸው ሌሎች አዋጆች ለቤተ ክርስቲያን ብዙ ጥቅሞች አስገኝተውላት ነበር። ከነዚህም መካከል ጥቂቶቹ፥ ቀደም ሲል የተወረሱ የቤተ ክርስቲያን ንብረቶች መመለስ፥ መንግሥት ቤተ ክርስቲያንን በገንዘብ መደጎም መጀመር፥ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ከማናቸውም ከመንግሥት ግዴታዎች ነጻ መሆን፥ በጠንቋዮችና በአስማተኞች ላይ እገዳ መተላለፍና 'የፀሐይ ቀን' (ሰንዴይ) እየተባለ የሚጠራው ቀን እሁድ፥ የዕረፍትና የክርስቲያኖች የአምልኮ ቀን እንዲሆን መደረጉ ናቸው። ሌላው ቀርቶ ዳናቲስትና አርዮሳውያንን ለማስታረቅ በ314 ዓ.ም. በአርልና በ325 ዓ.ም, በኒቅያ በተደረጉ ጉባኤዎች ቆስጠንጢኖስ እራሱን እንደ አንድ የሥነ-መለኮት ትምህርት መሪ በማድረግ ስብሰባውን በሊቀ መንበርነት መርቶ ነበር። በዚያን ጊዜ የክርስቲያኖች ቁጥር ከሕዝቡ አንድ አሥረኛ የማይበልጥ ቢሆንም በመንግሥቱ ዘንድ የነበራቸው ተደማጭነት ግን በእጅጉ የጎላ ነበር።

እንደተመለከትነው ቆስጠንጢኖስ ለቤተ ክርስቲያን ነጻነት ከመስጠቱና በብዙም ጉዳዮች ላይ ከቤተ ክርስቲያን ጎን የመቆሙን ያህል፥ በሌላ በኩል ቤተ ክርስቲያንን ለመንግሥቱ ታማኝ አገልጋይ በማድረግ ተጠቅሞበት ነበር። ከዚህም ሌላ በ330 ዓ.ም. የቁስጥንጥንያ ከተማ መመሥረት ምክንያት ሆኗል። ከተማው ለሮማ ግዛት በምሥራቅና ምዕራብ መከፈልና እንደዚሁም በ1054 ዓ.ም. ለተፈጠረው ለቤተ ክርስቲያን በሁለት ወገን መለያየት ምክንያት ሆኗል። ይሁን እንጂ በ5ኛው ክፍለ ዘመን ላይ የምዕራቡ ግዛት በጀርመን ነገዶች በወደቀበት ወቅት ይህ ከተማ ለግሪክ ሮም ባህል ጥበቃ ምቹ ስፍራ ሆኖ ነበር። ቁስጥንጥንያ የምሥራቁ የፖለቲካ ሥልጣን ማዕከል ለመሆን ከበቃበት ከ476 ዓ.ም. በኋላ የሮሙ ጳጳስ የራሱን የፖለቲካም ሆነ መንፈሳዊ ሥልጣን ይዞ ለብቻው ተገለለ።

የቆንስጠንጢኖስ ልጆች የአባታቸውን ፈለግ በመከተል ቤተ ክርስቲያንን የሚደግፍ ፖሊሲ ማራመድ የቀጠሉ ከመሆኑም፥ እንዲያውም መመሪያቸውን በማጠናከር የአረማዊነትን እምነት ወደ ተከላካይነት ደረጃ አስደረሱት። ከወሰዷቸው እርምጃዎች መካከል አንዱ የአሕዛብን መሥዋዕት የማቅረብ ሥርዓትንና በቤተ መቅደስ አምልኮ ውስጥ መገኘትን በሕግ ማገድ ነበር። ክርስትና በአጭር ጊዜ ውስጥ የመንግሥቱ ሃይማኖት እንደሚሆን እየተጠበቀ ሳለ ከ332-363 ዓ.ም. የኖረው ጁሊያን በ361 ዓ.ም. ሥልጣን በመያዙ ሂደቱን ገታው። ጁሊያን ክርስትናን በውጫዊ መንገድ እንዲቀበል የተገደደ ቢሆንም ቀደም ሲል የቅርብ ዘመዶቹ በክርስቲያን መሪ እጅ በመገደላቸውና እርሱም በአቴና የግሪክ ፍልስፍና በማጥናቱ የኒዮ-ፕሌተኒዝም ተከታይ ወደመሆን አዘነበለ። ቤተ ክርስቲያን የነበራትን የበላይነት መብት እንዲገፈፍ ካደረገ በኋላ ለሁሉም እምነቶች የነበረውን የእምነት ነጻነት እንደገና አወጀ። ሁኔታዎቹ ሁሉ የአረመኔን ፍልስፍናና ሃይማኖት ለማስፋፋት ተመቻቹ። ሆኖም ለቤተ ክርስቲያን መልካም አጋጣሚ የሆነለት የጁሊያን በሥልጣን ላይ መቆየት በአጭሩ በመቀጨቱ ሲሆን፥ የደረሰባትም ችግር ጊዜያዊና ቀላል ነበር።

1103. ከጁሊያን በኋላ የተነሡት ነገሥታት ግን ክርስትና ብሔራዊ ሃይማኖት እስኪሆን ድረስ ለቤተ ክርስቲያን የሚያደርጉትን እርዳታና አድልዎ ገፍተውበት ነበር። ለምሳሌ ንጉሠ ነገሥቱ ግሬሺን እንደዋና ካህን የሚጠራበትን የፓንቲፌክስ ማክሲመስ፥ ሥልጣኑን ካደ። ቴዎዶሲየስ 1ኛ በ380ና በ381 ክርስትናን የመንግሥቱ ብቸኛ ሃይማኖት የሚያደርገውን አዋጅ አወጣ። ከክርስትና ሌላ ሃይማኖት የአረማዊና የመናፍቅ ሃይማኖት ሲከተል ወይም ሲፈጽም የሚገኝ ሰው በመንግሥት ከባድ ቅጣት ይደርስበት ነበር። እንደዚሁም በ392 ዓ.ም. የታወጀው የቁስጥንጥንያ ድንጋጌ የአረማውያንን አምልኮ ፍጹም የሚቃወም ሆኖ ሳለ በ529 ዓ.ም. በጀስቲንያን የታወጀው ግን በአቴና የነበረውን የፍልስፍና ትምህርት ቤት እስከነጭራሹ እንዲዘጋ አደረገ። ይህም በአረማዊነት ላይ የተሰነዘረ የመጨረሻው የከፋ እርምጃ ነበር። ጁስቲንያን ከ483-565 ዓ.ም፡ የኖረና የታወቀው የምሥራቅ ንጉሠ ነገሥት (ከ527-565 ዓ.ም.)፥ በቁስጥንጥንያ የምትገኘው የቅድስት ሶፊያ ቤተ ክርስቲያን እንድትሠራ አደረገ። ኮርፐስ ጁሪስ ሲቪሊስ የተባለውን የሮም ሕግ በጽሑፍ አስሰፈረ። ይህ የብዙ ዘመናዊ የሆኑት አገሮች መሠረታዊ ሕግ ሲሆን፥ የቤተ ክርስቲያን ለካኖን ሕግ መሠረት ሆነ። የንጉሠ ነገሥት ጁስቲንያንና የሚስቱ ቴዎደራ ውብ የሆነ ግጥ የበዛበት ሞዚይክ (በተለያዩ ቁርጥራጭ በሆነ ድንጋይ ወይም መስታወት የተሠራ ሥዕል) በሳን ቪታሌ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በራቬና ይገኛል።

ክርስትና በጣም ጥቂት ተከታዮች የነበሩትና የተጠላ የእምነት ክፍል ከነበረበት ደረጃ ተነሥቶ የታላቁ የሮም መንግሥት ብሔራዊ ሃይማኖት ለመሆን ያስፈለጉትን ጠመዝማዛ መንገድ ልብ ብሎ ላጤነው፥ የጊዜው ሁኔታ መመቻቸት የሚዘነጋ ባይሆንም፥ ቤተ ክርስቲያን በግሏእ ያደረገችው ከፍተኛ ጥረት ግን ወሳኝ ሚና መጫወቱን መገንዘብ አያዳግተውም። ክርስትና የኅብረተሰቡን የሥነ-ምግባር ደረጃ ከፍ ስለማድረጉ ብዙ የማይታበሉ ሐቆች አሉ። በማስረጃነትም፥ ለሴቶች መብት በኅብረተሰቡ ወስጥ የተሻለ ትኩረት መስጠቱ፥ የተለያዩ የጭካኔ ግድያዎችን የሚያሳዩ ትርእኢቶች መቆማቸው፥ በባሪያዎች ይደርስባቸው የነበረው አሰቃቂ በደል እየቀነሰ መምጣት፥ የሮም ሕግጋት በበለጠ በፍትህ ላይ የተመሠረቱ መሆኑ፥ እና የሚስዮናዊነት ሥራ መስፋፋት በግንባር ቀደም የሚጠቀሱ ናቸው። ይሁን እንጂ ይህ የቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ጋር የቅርብ ግንኙነት ማድረግ ጥቅም ያስገኘውን ያህል በቀላሉ የማይገመት ጉዳትም እንዳስከተለ መረዳት ያሻል። መንግሥት ለቤተ ክርስቲያን በሰጠው ክብር፥ ጥበቃና እርዳታ አጸፋ በምላሹ በመንፈሳዊና በሥነ-መለኮት ትምህርት ጉዳይ ጣልቃ እንዲገባ ይፈቀድለት ዘንድ መጠየቅ ጀመር። ቆስጠንጢኖስ የዓለማዊው የሮም መንግሥት መሪ ቢሆንም እንኳን፥ በ314 ዓ.ም. በአርልና በ325 በኒቅያ በተካሄደው ጉባኤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተፈጠረውን ውዝግብ ለመዳኘት እራሱን መንፈሳዊ ዳኛ አድርጎ ነበር። ውሎ ሲያድር በመንግሥትና በቤተ ክርስቲያን መካከል እየከረረ ለሄደው አሳድካሚና አሰልቺ ውዝግብ መንሥኤው ይህን የመሰለው ድርጊት ነበር። ሌላው ብዙ ትዝብት ለማትረፍ ያበቃው ጉዳይ ቤተ ክርስቲያን ሥልጣን በምታገኝበት ጊዜ ልክ የአረማውያን ባለሥልጣናት በክርስቲያኖች ላይ ይፈጽሙት የነበረው ዓይነት ግፍ እርሷም በአረማውያን ላይ ለመፈጸም መሞከሯ ነው። በመሆኑም ሁኔታዎች በሚዛናዊነት ዓይን ሲታዩ በመንግሥትና በቤተ ክርስቲያን መካከል የተፈጠረው የቀረበ ግንኙነት ካስገኘው በረከት ይልቅ ጉዳቱ እንደሚብስ ነው።

## II. ቤተ ክርስቲያንና ባርቤሪያን (አረማውያን)

እርግጥ በ4ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት መስማማቷ መልካም አጋጣሚ ነበር ለማለት ይቻላል። ምክንያቱም የዚህ ክፍለ ዘመን መጨረሻ በኋላ ላይ እንደምንመለከተው በአውሮፓ ውስጥ አዲስና ከፍተኛ ችግርን ያስከተለ በመሆኑ ነው። ችግሩም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ 11ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ያለማቋረጥ ወደ አውሮፓ በመፍለስ ላይ የሚገኙትን አሕዛብ ወደ ክርስትና ለመለወጥ ከሚደረገው ጥረት የመነጨ ነበር። ከ375-1066 ዓ.ም. በነበሩት ምዕተ ዓመታት ቁጥር ስፍር የሌላቸው የቱቶናውያን፥ የቫይኪንግያውያን፥ የሰላቫውያንና የሞንጎል ነገዶች ወደ አውሮፓ አካባቢ ይፈልሱ ነበር።

### ሀ. የባርቤሪያን መስፋፋት

ባርቤሪያን ጎዞ የሚባሉት በሮም መንግሥት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የታዩት በዳንዩብ የወሰን ክልል አካባቢ በመጨረሻ 4ኛው ክፍለ ዘመን ነበር። ሆኖም የሞንጎል ነገዶች ከኋላቸው ያሳድዷቸው ስለነበር ወደ ሮም ግዛት ዘልቀው ለመግባት ከማዕከላዊው መንግሥት ፈቃድ ጠየቁ። ይህም ባስከተለው አለመግባባት ሳቢያ በእነርሱና በሮማውያን መካከል በ378 ዓ.ም. የተካሄደው የአድርያኖፕል ጦርነት የጎትሠ

ንጉሥት ቫለንስን ሞት ከማስከተሉም፥ ለእነኝህ ለአሪዮሳውያን ቪዚጋት [ምዕራባውያን ጎዝስ] በመንግሥቱ ምሥራቃዊ ክፍል መስፋፋት ምክንያት ሆነ። ብዙዎቹም የነርሱ ወገኖች ከጦርነቱ በኋላ የዳንዩብን ወንዝ እያቋረጡ መፍለሳቸውን በመቀጠል በ410 ዓ.ም. ሮምን አሸንፈው አገሪቱን ለመበዝበዝ በቁ። ከዚያም በ426 ዓ.ም. አካባቢ በእስፔይን የራሳቸውን መንግሥት መሠረቱ። አርዮሳውያን ቫንድሎች የባርቤሪያን ጎዝ ፈለግ በመከተል ከምሥራቅ የራይን ወንዝ ጀምሮ መጨረሻ እስከሠፈሩበት ሰሜን አፍሪካ ውስጥ ደረሱ። አሪዮሳውያን ኦስትሮጎቶች በመባል የሚታወቁት ሌሎቹ የጎዝ ነገዶች ደግሞ በሮም ግዛት በቴዎዶሪክ መሪነት ሌላ መንግሥት አቋቋሙ። እንደዚሁም ቫንድሎች በሰሜን አፍሪካ፥ አሪዮሳውያን የሆኑት ሎምባርዶችና ቡርግንዲያኖች አረማዊ ከሆኑት የፍራንክስ ነገዶች ጋር በመተባበር የአሁኒቱ ፈረንሳይ ተብላ በምትጠራው አገር ላይ ሰፈሩ። አንግሎ ሳክሶናውያን በበኩላቸው እንግሊዝን ወረሩ። በዚህ ክፍለ ዘመን በምዕራብ አውሮፓ የነበረችዋ ቤተ ክርስቲያን ይህን ሁሉ ችግር ያሳለፈችው ብትሆንም፥ ለአጭር ጊዜም ቢሆን በአቲላ መሪነት አውሮፓን ለመውረር ተነሥተው የነበሩትን የሞንጎል ሀን ወራሪዎች በተጨማሪ መቋቋም ነበረባት። ሆኖም እነዚህ ወራሪዎች በ451 ዓ.ም. ቻሎንስ በተባለ ስፍራ በተገኘ ድል ተባረሩ። ከዚያም በኋላ በሰፊነው ጊዜያዊ ድል በመጠቀም ቤተ ክርስቲያን አብዛኞዎቹን የቱቶናውያን ነገድ ሕዝቦች ለክርስትና ለማሸነፍ ስትችል፥ በ6ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ከአርዮሳውያን ሎምባርዶችና ከእስላሞች አዲስ የወረራ ፈተና ገጥሟአት ነበር።

1104. በእነኝህ ዘመናት ውስጥ ምዕራብ አውሮፓ ከተያያዘችው ከፍተኛ የሥልጣኔ ምዕራፍ የተደረሰው አውሮፓን ዳር እስከዳር በወረርዋት በነዚህ ባርቤሪያውያን ነገዶች ልዩ ተሰጥኦና ጉብዝና ሳይሆን፥ ቤተ ክርስቲያን ባደረገችው ያላቋረጠ ጥረት ወደ ክርስትና እምነት ልታመጣቸው በመቻሏ ነው።

ካርታ - ገፅ 120

የባርቤሪያኖች መሪና የጀርመናዊ ነገዶች መንግሥታት፦ - ቪዚጎትስ - ኦስትሮጎትስ - ፍራንክስ - ቫንዳልስ - ቡልኔሪያንስ - ሀንስ - የምሥራቁ መንግሥት

ለ. ወንጌልን ለባርቤሪያንስ የማድረስ ሥራ

አርመኒያ (አርመን) ለወንጌል በሯአን የከፈተችው በ301 ዓ.ም. አካባቢ ጎርጎሪዮስ ኢሉሚኔተር በሚባለው (የወንጌል አስተማሪ) አማካይነት ንጉሥ ታሪዳትስ የክርስትናን እምነት ከተቀበለና ከተጠመቀ በኋላ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ በአርመንኛ ቋንቋ በመተርጎሙም በ433 ዓ.ም. አያሌ ሚሊዮን የሚደርሱ ሰዎች ለክርስትና ተሸነፉ። በብሔራዊ ደረጃ በግልጥ ክርስቲያን ከሆኑ መንግሥታት የመጀመሪያው አርመኒያ ስትሆን፥ ሕዝቦቿአ ለዘመናት ሁሉ ስደትና መከራ ቢገጥማቸውም፥ እምነታቸውን አጥብቀው እንደያዙ የሚገኙ ናቸው።

እንደዚሁም ፍሬምናጦስ (ከ300-380 ዓ.ም አካባቢ) በግሪክ ወደምትገኘው ጢሮስ እንደ ባሪያ ሆኖ ሲመጣ፥ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ነጻ ሆነ። ኢትዮጵያውያን ኦርቶዶክስ (ኮፕቲክ) ክርስቲያን እንዲሆኑ አደረገ። የእስክንድርያው ጳጳስ አትናቴዎስ፥ ፍሬምናጦስን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ አድርጎ ከሾመው ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከግብፅ በሚላኩ ጳጳሳት ለብዙ ዘመናት ስትመራ ከቆየች በኋላ፥ በ1957 ዓ.ም እራሷን ቻለች።

የብሪታንያ ደሴቶችም በዚህ ዘመን ነበር ለክርስትና የተሸነፉት። ሴልቲክ ዝርያ ለሆኑት ብሪታኒያውያን ክርስትና እንዴት እንደደረሰ የምናውቀው ነገር ባይኖርም ምናልባት በሮማውያን ሰፋሪዎችና ነጋዴዎች አማካይነት ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለ። በተረፈ ግን ሦስት የሴልቲክ ጳጳሳት በ314 ዓ.ም. በአርል በተደረገው ጉባኤ የሴልቲክን ቤተ ክርስቲያን ወክለው እንደተገኙ ይነገራል። እንደዚሁም የአውግስጢኖስ ተቃዋሚ የነበረው ፔሌጂየስ የመጣውም ከሴልቲክ ቤተ ክርስቲያን ሲሆን በስሙ ይታወቅ የነበረውን የሐሰት ትምህርት (ኑፋቄ) በ410 ዓ.ም. አካባቢ ማስተማር መጀመሩ የተረጋገጠ ነው። ይህች ጥንታዊትዋ በእንግሊዝ የነበረች የሴልቲክ ቤተ ክርስቲያን የሮምን ጳጳስ የሥልጣን በላይነትንም ሆነ ተቀዳሚነት አላትቀበልም ነበር። የፋሲካ በዓል የሚከበርበትን ቀን በመወሰን ሂደት ውስጥ የተከተለችው የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያንን ልምምድ ሲሆን፥ ከሮሚአ ቤተ ክርስቲያን የማትስማማባቸው ሌሎችም ያልጎሉ የልዩነት ምልክቶች ነበሩ። በ5ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ፥ በብሪታንያ የነበረው የሮም ሠራዊት በሮም መንግሥት ምሥራቃዊ ወሰን ክልል የተፋፋመውን የባርቤሪያኖች ወረራ ለመከላከል ለቆ በመውጣቱ፥ ይህቺ የሴልቲክ ቤተ ክርስቲያን ያለምንም ጠባቂ ቀረች። የሴልቲክ ሕዝቦችም አረማውያን በነበሩት የአንግለውያን፥ የሳክሰንና የጁትስ ነገዶች ሲደመሰሱ የተረፉት ወደ ምዕራባዊውና ሰሜናዊው የአገሪቱ ተራራማ ክፍሎች ተባረሩ።

1105. በጎዝ ነገዶች መካከል የሚስዮናዊነት ሥራ የተጀመረው ደግሞ ቪዚጎት ገና የዳንዩብን ወንዝ አቋርጠው ወደ ሮም መንግሥት ግዛት ከመግባታቸው በፊት ነበር። የአርዮሳዊ የክርስቲያን ዘርፍ ተከታይ የነበረው ኡልፍለስ (311-81 አካባቢ) በእነዚህ ሕዝቦች መካከል የሚስዮናዊነት ተግባር ለመፈጸም መንፈሳዊ ጥሪ እንደደረሰው ተሰማው። እርሱም የመጀመሪያ የጎዚክ ክርስቲያን ጳጳስ ሆኖ በመቀባት ሕይወቱን አብሯቸው ለማሳለፍ ቆረጠ። በአገልግሎቱ በጣም ውጤታማ ከመሆኑ የተነሣ ጎዝስ የሮምን ግዛት በወረሩበት ወቅት አብዛኞዎቹ ክርስቲያን ሆነው ነበር። ኡልፍለስ የጎዞችን ቋንቋ ለጽሑፍ ወደሚመች ፊደል በመቀየርና ቅዱሳት መጻሕፍትን በመተርጎም፥ ነገዶቹን በራሳቸው ቋንቋ የተጻፈ መጽሐፍ ቅዱስ ባለቤት ለመሆን ከማስቻሉም እርሱም የመጀመሪያው እውቅ ሚስዮናዊ ተርጓሚ ተብሎ ለመጠራት በቅቷል። እነኝህ ነገዶች ጦርነት የሚወዱ ሕዝቦች ስለነበሩ የብሉይ ኪዳንን የነገሥታት መጻሕፍት በቋንቋቸው መተርጎም አስፈላጊ አይደለም ሲል ኡልፍለስ አምኖበት ነበር። ያም ሆኖ ጎዝ ኡልፍላስ ለመሰከረላቸው የአርዮሳውያንን ዘርፍ የክርስትና እምነት ተከታይ ሆኑ። ስለዚህም ነው የምዕራቧአ ቤተ ክርስቲያን የኋላ ኋላ ከባድ ኃላፊነት አሕዛብን ከአረማዊነት ወደ ክርስትና ማምጣት ብቻ ሳይሆን የአስፔይን ቪዚጎቶችና ላምባርዶችን ከአርያኒዝም ወደ ትክክለኛው ክርስትና መመለስ ጭምር ለመሆን የቻለው።

በሌላም በኩል የራይንን ወንዝ አቋርጠው የመጡት አረማውያን የሆኑ የቴዩታኒክ ወራሪዎች ለምዕራብ ቤተ ክርስቲያን የበለጠ ውጥረትና ችግር ለማስከተል በቅተው ነበር። ማርቲን አፍ ቱርስ የሚባለውና (335-400 አካባቢ) በአሁኑ ጊዜ የፈረንሳይ ታዳጊ (ቅዱስ ጠባቂ) ሆኖ የሚቆጠረው ሌላው ሚሲዮናዊ በደቡብ ጎል ለሰፈሩት ለቡርግንዲያ ዝርያዎች ወንጌልን የመስበክ ጥሪ ለእርሱም እንደደረሰው አምኖ ነበር። ወንጌልን ለእነዚህ ሕዝቦች ለማዳረስ ከዚህ በፊት ባልታየና ልዩ በሆነ ዘዴ ለመጠቀም ወሰነ። ዘዴውም ተከታዮቹን መነኮሳት በወታደርነት በማሠልጠንና በቡድን በማደራጀት የጣዖት አምልኮት ስፍራዎችን እንዲያጠፉ በማድረግ ነበር። ይህ አስደናቂ ተግባሩ እንደ አውግስጢኖስ በታሪክ ሳይዘከርለት ወይም ዝናን ሳያተርፍለት የቀረው የቡርግንዲያኖች የሃይማኖት ታሪክ ወንድሞቻቸው በሆኑትና በዚሁ በጎል ግዛት አብረዋቸው በሰፈሩት ፍራንኮች (ፈረንሳዮች) ታሪክ ገናናነት ተውጦ በመቅረቱ ነው።

ቱርሱ ጎርጎርዮስ (ከ538-94 ዓ.ም አካባቢ) ስለፍራንኮች በጻፈው ታሪክ ውስጥ እነኝህ ነገዶች በጎል ውስጥ እንዴት እንደሰፈሩ፥ እንዴትስ ወደ ክርስትና እምነት እንደተለወጡና የቀድሞ ታሪካቸውንም ጭምር በማስመልከት ጥሩ ዘገባ አቅርቧል። በ5ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ክሎቪስ (481-511 ዓ.ም አካባቢ) የተባለው የፍራንኮች ንጉሥ፥ ክርስቲያኒ የሆነችውን ቡርግንዲዋን ልዕልት ክሎቲልዳ አግብቶ ነበር። ስለዚህ በእርሷአም ተፅእኖ ሌላ ክሎቪስ በገጠመው ጦርነት ላይ ድልን በመቀዳጀቱ ለዚህ ያበቃው መለኮታዊ ኃይል እንደሆነ በማመን በ496 ዓ.ም. ወደ ክርስትና እምነት ተለወጠ። እርሱም ክርስቲያን በሆነበት ዕለት አብዛኛው የፈረንሳይ ሕዝብ ክርስትናን ተቀበለ።

ይህ የአብዛኛው ሕዝብ ክርስትናን መቀበል በእውነተኛ መረዳት ይሁንም አይሁንም የክሎቪስ ክርስትናን መቀበል ግን ለቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከፍተኛ ጠቀሜታ አስገኝቷል። ዛሬ ፈረንሳይ እየተባለች የምትጠራውን የቀድሞይቷን ጎል በአብዛኛው የያዙት ፍራንካውያን በሙሉ በክርስትና ሥር ለመሆን በቅተዋል። ሚሲዮናውያንም ከዚች ከጎል ተነሥተው ነበር ወደ አርዮሳውያን እስፔይን በመሄድ ፊታቸውን ከእውነተኛው ክርስትና ትምህርት ያዞሩበትን አርዮሳውያን ጎቶች ለመመለስና ለማሸነፍ ከፍተኛ ተጋድሎ ያካሄዱት። ከሁሉም በላይ ደግሞ የፍራንኮች የንጉሥዊ አገዛዝ መንግሥት በመካከለኛው ዘመን ውስጥ ሁሉ ለሮም ጳጳሳት (ፓፖሲ) ከፍተኛውና የማያወላውል ደጋፊው ነበር። የፍራንኮች ነገሥታት በደቡብ አውሮፓ የሚገኘውን የአልፕስ ተራራ አቋርጠው ወደ ኢጣሊያን በመዝለቅ፥ የሮሙን ጳጳሳት ብዙ ጊዜ ከተነሡባቸው ጠላቶቻቸው አስጥለዋቸዋል።

የኋላ ኋላም የአየርላንድ ታዳጊ (ቅዱስ ጠባቂ) ለመቀበል የበቃው ፓትሪክ፥ (389-461 አካባቢ) ከብሪታኒያ ወደ አየርላንድ በ16 ዓመቱ በባሕር ላይ ወንበዴዎች ተጠልፎ የተወሰደ ነበር። ከዚያም ከብቶችን በመጠበቅ 6 ዓመታት ያህል አሳለፈ። ወደ አገሩ ከተመለሰ በኋላ በአየርላንድ ሚሲዮናዊ ሆኖ ለማገልገል መንፈሳዊ ጥሪ እንደደረሰው ተሰማው። ከ432-461 ዓ.ም. ባለው ጊዜ በአየርላንድ ለሚገኙት ሴልቶች ወንጌልን በመስበክ ላይ እንዳለ ከድሩይድ ሃይማኖት ካህናት ከፍተኛ ተቃውሞ ቢገጥመውም ደሴቷን በመጨረሻ ላይ ጠንካራ የሴልቲክ ክርስትና ደሴት ሊያደርጋት ችሏል። በጎሳዎች ስፍራ የሚኖሩ ክርስቲያኖች በገዳማት ዙሪያ በመሆን እንዲቋቋሙ አደረገ። በአውሮፓ የጨለማ ግዛት ዘመን እየተባለ የሚጠራው አስከፊ ውድቀት በደረሰበት ጊዜ፥ አየርላንድ በአህጉሪቱ ለሚላኩ ሚሲዮናውያን መነኮሳት እንደ የባህልና የምሁራን ማዕከል ሆና አገልግላ ነበር። ኮሎምባ ስኮቶችን (ስኮትላንድን) ለክርስትና ለማሸነፍ የተነሣው ከአየርላንድ ነበር።

ፓትሪክ የአየርላንድ ሐዋርያ ተብሎ እንደሚጠራው ሁሉ ኮሎምባም (521-597) የስኮትላንድ ሐዋርያ ነበር። በ563 ዓ.ም. በአዮና ደሴት ላይ በመላው ስኮትላንድ ወንጌል ለማድረስ ማዕከል የሚሆን አንድ ገዳም አቋቋመ። አይዳን በ635 ዓ.ም. ኖርተምብሪያን ለወረሩት የአንግሎ ሳክሶን ዝርያዎች ወንጌልን ለመስበክ የተነሣው ከዚሁ ገዳም ነው። አየርላንድና በስኮትላንድ የተመሠረተችው ይህች የሴልቲኳ ቤተ ክርስቲያን ከሁሉም በላይ ሚሲዮናዊ ነበረች።

በዚህ በምንወያይበት 6ኛ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ የሴልቲክ ክርስትና በስኮትላንድና በአይርላንድ ባለድል ሲሆን ከእንግሊዝ ምድር ግን ጠፍቶ ነበር። ይሁን እንጂ የሴልቷና የሮም ክርስቲያኖች አንግሎ ሳክሶኖችን ለክርስትና ለማሸነፍ በየግላቸው በመጣር ኃይለኛ ተፎካካሪዎች ሆነው የታዩበት ይህ ክፍለ ዘመን ነው።

በ590 ዓ.ም. ላይ ቤተ ክርስቲያን በሮም መንግሥት ከሚደርስባት ስደት ነጻ መሆን ብቻ ሳይሆን በጊዜው ከነበረው መንግሥት ጋር የቅርብ ግንኙነትም ነበራት። ከዚህ ሌላ የቴዩታኒክ ወራሪዎችን ወደ ክርስትና እምነት ለመለወጥና የግሪክና የሮም ባህልና ሥልጣኔን ለማስተላለፍ የራሷን ድርሻ ተወጥታለች። በዚህ ሂደት ውስጥ ብዙ አረማውያን በፍጥነት ለክርስትና እምነትም ስለተሸነፉ እነርሱን ማሠልጠንና የፈተና ጊዜያቸውን እስኪያልፉ አመራር መስጠት ለቤተ ክርስቲያን ከአቅሟ በላይ የሆነ ሥራ ነበር የሆነባት። ስለዚህ ብዙዎቹ አዲስ አማኞች የቀድሞውን አሮጌ የሕይወት አኗኗርና ልማዳቸውን በመያዝ ከቤተ ክርስቲያን ተደባለቁ። ቀድሞ ያደርጉት የነበረውን ጀግናን የማምለክ ልማድ ቅዱሳንን ወደ ማምለክ ለወጡት። በርካታ አረማዊ ሥርዓቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሰርገው ለመግባት መንገድ አገኙ። ቤተ ክርስቲያን የባርቢራውያንን ፍላጎት ለማሟላት የወሰደችው የተቻኮለ እርምጃ በተራው እራሷንም በአንዳንድ የአረማዊነት አምልኮዎች ለመጠናወት ዳረጋት።